# ወደኋላ የተጓዘው አዲሱ የፕሬስ ሕግ

ከአምስት ዓመታት በፊት አሁን በሥራ ላይ ያለውን የ1985 የፕሬስ ሕግ ለማሻሻል በሚል ለውይይት ሲቀርብ ጋዜጠኞች ተቃውሞአቸውን በአንድ ድምፅ አሰሙ። ረቂቅ ሕጉ የፕሬስ ነፃነቱን አደጋ ላይ የሚጥል ነው ብለው ተከራከሩ። ረቂቁም ተወካዮች ምክር ቤት ሳይላክ ምርጫ 97 መጣ።

ከምርጫው በፊት ጠንካራ ተቃውሞ ካስነሱ ነገሮች አንዱ የዚህ ሕግ መረቀቅ የነበረ ቢሆንም፣ በዚያ ግርግር ሕጉን ለማፀደቅ የጠየቀ አንድም የመንግሥት አካል አልነበረም። ነገር ግን በ1997 ዓ.ም. አዲሱ የወንጀል ሕግ ሲወጣ ከረቂቁ ላይ የተወሰኑ አንቀጾች ተወስደው "በመገናኛ ብዙኃን አማካኝነት በሚደረጉ ወንጀሎች ተካፋይ ስለመሆን" በሚል አንቀጽ ስር የወንጀል ሕግ ሆኖ ፀደቀ።

በ1999 ዓ.ም. አጋማሽ ላይ የፕሬስ ሕጉ ሊፀድቅ ነው የሚሉ ጭምጭምታዎች መሰማት ሲጀመር ፓክት ኢንተርናሽናል የተባለ ድርጅትም ጋዜጠኞች በሕጉ ላይ የሚነጋገሩበት መድረክ ይፈጠር በሚል በየሣምንቱ ማክሰኞ የሚካሄድ ፎረም አዘጋጀ። ወቅቱ ብዙ ጋዜጠኞች ከቅንጅት አመራሮች ጋር የታሰሩበት ነበርና አብዛኛው ጋዜጠኛ ታስሮ እንዴት ሁሉን ያካተተ ውይይት ይደረጋል የሚል ሃሳብ ተነስቶ ትንሽ ካጨቃጨቀ በኋላ የተወሰኑ ጋዜጠኞች በፎረሙ ሲሳተፉ የተወሰኑት ደግሞ አቆሙ። ፎረሙ የተለያዩ አጀንዳዎችን እያነሳ ውይይት ለማድረግ የመነሻ ሃሳብ ቢያቀርብም የፕሬስ ሕጉ እንዲሻሻል ግፊት ቢደረግ ይሻላል በሚል ተጀመረ።

እናም "የመንግሥት ተለጣፊ ናቸው" የሚል ስያሜ ያላቸው ማኅበራት ፎረሙን ተቀላቅለው ሕጉን በሚመለከት ከመንግሥት ጋር ውይይት ለማድረግ ሲንደረደሩ የተቀሩት ደግሞ አባላቶቻችንን አወያይተን ካልሆነ መሳተፍ አንችልም፣ ለዚህ ደግሞ ገንዘብ እንፈልጋለን ሲሉ በሃሳብ ተለዩ። የቀሩትም ተሳክቶላቸው አባላቶቻችን ናቸው ያሏቸውን ሰብስበው አወያዩ፣ በመጨረሻም በፓክት ኢንተርናሽናል አማካኝነት ጥሪ የተደረገላቸው ጋዜጠኞች በተገኙበት ስምምነት ያላገኘ ውይይት ተካሄደ።

ከፓክት ኢንተርናሽናል ውይይት በፊት ግን ይኸው የፕሬስ ሕግ በበርካታ የሚዲያና የሕግ ባለሙያዎች የሰላ ትችት ሲቀርብበት የቆየ ከመሆኑም በላይ በወደፊቱ የኢትዮጵያ ነፃ ፕሬስ ዕጣ ፈንታ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተጽዕኖ ከፍተኛ መሆኑን ሲነገርለት ቆይቷል።

የሕጉን ጠንካራና ደካማ ጐን ሲፈትሹ የቆዩ የሕግ ባለሙያዎችና ጋዜጠኞች ሕጉ ከ1985ቱ የፕሬስ ሕግ የሚሻልበት አንዳንድ ነጥቦች መኖራቸውን ጠቁመው፣ በተቃራኒው

ከ1985ቱ እጅግ የከፋ እና ሕገመንግሥታዊ መብቶችን የሚጋፋ ሕግ መሆኑን አንቀጽ በአንቀጽ እየጠቀሱ ተከራክረውበታል።

ከሕጉ ጠንካራ ጐኖች መካከል፤ የፕሬስ ሕግን በመተላለፍ ለሚፈጸሙ የወንጀል ተግባራት የእስር ቅጣት እንዲቀር ማድረጉ፣ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ላይ መረጃ የመስጠት ግዴታ መጣሉን እና የተጠየቁትን መረጃ ከመስጠት በስተቀር ለምን ዓላማ እንደሆነ እንኳን መጠየቅ አይችሉም ተብሎ መደንገጉ ተጠቃሽ ነው።በአንጻሩም ይኸው የፕሬስ ሕግ የሕጐች ሁሉ የበላይ የሆነውን ሕገመንግሥቱን ይቃረናል የተባለበት አንቀጾች ማካተቱን አንድ በአንድ ተመልክቷል።

ለምሳሌ በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 29 (3) በማንኛውም መልኩ የቅድሚያ ምርመራ (ሴንሰርሽፕ) የቀረ መሆኑን ቢደነግግም፣ በአሁኑ የፕሬስ ሕግ ግን በጋዜጠኛው ሃሳብን የመግለጽ መብት ላይ በተለየ መልኩ የራስ ገደብ (የሰልፍ ሴንሰርሺፕ) ድንጋጌን ይዞ መምጣቱ፣ የፕሬስ ሕጉ እና የመረጃ ሕጉ አንድ ላይ መውጣቱ፣ የመገናኛ ድርጅቶች አመሠራረት በኩባንያ መልክ ብቻ እንዲሆን መገደቡ፣ ከፕሬስ ጋር በተያያዘ ለተፈጸመ ወንጀል ከፍተኛ ቅጣት መጣሉና በተጨማሪም ካሣ እንዲከፍል መደረጉ፣ ጋዜጠኛውን በማያስፈልግ የራስ ገደብ (ሰልፍ ሴንሰርሺፕ) ውስጥ እንዲገባ የሚያደርገው መሆኑ ተዘርዝሯል።

ይሁንና ሕግ አርቃቂዎቹ በፕሬሱ በተለይም በነፃው ፕሬስ ላይ ባላቸው የተዛባ አመለካከት የተነሳ ሊያሻሽሉ የሚገባቸውን ረቂቅ ሕግ በማሻሻል ፈንታ ጨርሰውኑም በሕጉ የመጨረሻ ደረጃ ላይ አሳሪ የሆኑ ድንጋጌዎች ማካተታቸው፣ መላውን የመገናኛ ብዙኃን አባላት እና ባለድርሻዎቹን አሳዝኗል።

አሁንም አንዳንድ ካድሬ የመንግሥት ጋዜጠኞችና ማኅበራት ስለ ሕጉ ወርቃማነት እየተናገሩ ቢሆንም የዚህ ሕግ አሉታዊ ይሁን አዎንታዊ ተጽዕኖ አሁን ባሉበት ሁኔታ ስለማይመለከታቸው “በሉ የተባሉትን ቢሉ” የሚገርም አይሆንም።

በዚህ ሣምንት የጋዜጠኞችን አጀንዳም ስለዚሁ ገዳቢ የፕሬስ ሕግ ጋዜጠኞች ራሳቸው ምን ይላሉ? ምንስ የመፍትሔ ሃሳብ አላቸው? ብለን ሦስት ጋዜጠኞችን አነጋግረናል። የመጀመሪያው አቶ አማረ አረጋዊ የሪፖርተር ጋዜጣ ዋና አዘጋጅና ባለቤት ሲሆኑ ከ1995 ዓ.ም. ጀምሮ ይኸው የፕሬስ ሕጉ ሳይሻሻል እንዳይፀድቅ በተለያየ መድረክ ሲከራከሩ ከቆዩ ሰዎች አንዱ ናቸው። እናም አዲሱ የፕሬስ ሕግ ቀደም ካለው የፕሬስ ሕግ ምን ያህል ተሻሽሎ እንደወጣ ለጠየቅናቸው ሲመልሱ “መሻሻል ያለበትን ያህል ተሻሽሎ ወጥቷል ሳይሆን፣ በሚገርም ሁኔታ በመጨረሻ ደረጃ ላይ ያልተጠበቁ ሦስት፣ አራት አንቀጾች ያህል እንደገና ገብተው ተገኝተዋል። እና በአጠቃላይ በእኔ አስተያየት፣ ይኼ ሕግ ለአገራችን የፕሬስ ኅልውና አደገኛነቱ ይታየኛል። በአሁኑ ጊዜ በዓለም ደረጃ

በተለይም በአፍሪካ አገራት የፕሬስ ሕጋቸውን በማሻሻል አያሌ የፕሬስና የብሮድካስት ዕድገት እያስመዘገቡ ይገኛሉ። እኛም በዚህ መንፈስ ያሉብንን ድክመቶች እያረምን፣ ለተሻለ የፕሬስ ዕድገት መጣር ይኖርብናል።" ብለዋል።

አቶ አማረ መጥፎ ፕሬስ ወይም መጥፎ ጋዜጣ የለም ብለው እንደማያምኑ ይናገራሉ፤ "መጥፎ ጋዜጣ አለ ተብሎ ግን መጥፎ ሕግ አይወጣም። በጋዜጣዊ ነፃነቱ ላይም ውጊያ አይከፈትበትም። የጐርፍ አደጋ ደረሰ ተብሎ ፀረ ዝናብ አይኮንም፣ ጎርፉን ለመከላከል ነው ጥረት መደረግ ያለበት" ባይ ናቸው።

አሁን ባለው ሁኔታ፣ ፕሬሱ ወደፊት ሊገጥሙት የሚችሉ ተግዳሮቶች እንዳሉ አቶ አማረ ይገምታሉ። ነገር ግን ትክክለኛ ፕሬስ ሆኖ ከመቀጠል ሳይቆጠቡ የተሻለ የፕሬስ ነፃነት እንዲመጣ መታገል የሞያ ግዴታ ነው ብለው እንደሚያምኑ ነው የተናገሩት።

አቶ አማረ ስለ ፕሬሱ ውስጣዊ ችግር ሲያብራሩም "እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ ፕሬስ አንደኛው ችግር አስቸጋሪ የፕሬስ ሕግ መውጣት ያለመውጣቱ አይደለም፤ ፕሬሱ ራሱ በተለያየ አቅጣጫ በችግር ተተብትቧል። ለምሳሌ እንደ አሁኑ በመንግሥት በኩል መጥፎ የፕሬስ ችግር አጋጥሞታል፣ በራሱም ደግሞ ለፕሬስ ነፃነት የቆመ አይደለም። የፕሬስ ነፃነት ዓይነተኛ ዓላማ እኮ ሃሳብ በነፃነት ይንሸራሸር ነው። የኢትዮጵያ ፕሬስ ግን በተቃራኒው ሃሳብ በነፃነት መንሸራሸር የለበትም ባይ ነው። የእኔን ሃሳብ ዓይነት ካላሰብክ የትኛውንም ሃሳብ መስማት የለብኝም እያለ ነው። ስለዚህ ከዚህ መሰል መሠረታዊ ስህተቱ ተምሮ ከቀጠለ እርግጠኛ ነኝ የተሻለ የፕሬስ ነፃነት ይመጣል ብዬ አምናለሁ" ይላሉ።

አቶ አማረ አዲሱ የፕሬስ ሕግ ካለፈው የተሻሉ ነገሮች እንደተካተቱበት አልሸሸጉም። ለምሳሌ የጋዜጠኞች ለምርመራ መታሰርን ማስቀረቱ ተጠቃሽ ነው። ግን ይኼም ቢሆን "200 ሺህ ብር እንድትቀጣ ተወስኖብህ ባትከፍል መታሰሩ ላይቀርልህ ይችላል፤ ለዚህም ነው አንዳንድ ተሻሽለው መጡ የተባሉ ነገሮች ምንም ተሻሻሉ እንደማይባሉ የምንናገረው" ብለዋል።

በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 29 ሃሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት የተቀበለ መንግሥት፤ እንደገና ዞር ብሎ የአሁኑን ዓይነት የፕሬስ ሕግ ያወጣል ብሎ የገመተ የለም የሚሉት አቶ አማረ፤ "የፕሬሱ ሕጉ ተሻሽሎ ወጥቷል ቢባልም ተሻሽለው የወጡት ነገሮች ግን አሉታዊ የሆኑ ትርጓሜዎችን ይዘው እንደወጡ ነው ያየነው" ብለዋል።

ይሻሻሉ ተብለው ሃሳብ የተሰጠባቸው የፕሬሱ ረቂቅ ሕጐች ቀርተው የሕግ አውጪው ሃሳብ ብቻ መጽደቁ ለምን እንደሆነ ለጠየቅናቸውም "በመሠረቱ በዚህ ሕግ ላይ የሚመለከታቸው ወገኖች አስተያየት ተካተተበት ማለት ለሚወጣው ሕግ ዋስትና ነው ማለት አይደለም። አንድ ሰው በአንድ ነገር ላይ ለሌላ ሰው አስተያየት ሰጠ ማለትም አዳመጠው ማለት አይደለም። ስለዚህ መናገር ሌላ ነው፣ መደመጥ ሌላ ነው" ብለዋል።

የፕሬስ ነፃነት መሠረታዊ ሰብዓዊ መብት እንጂ "እንዴ ልናገር" ተብሎ ፈቃድ የሚጠየቅበት ጉዳይ ባለመሆኑ፤ ከዚህ በኋላም ጠንካራ የፕሬስ ነፃነት ለመፍጠር ጋዜጠኛው ራሱ ተባብሮ ለፕሬስ ነፃነት መቆም እንዳለበት ይመክራሉ።

ጠንካራ ፕሬስ ከመፍጠር አኳያ የተወሰነ ርቀት ለመሄድ ቢቻልም ችግሮቹም በቀላሉ የሚነገሩ እንዳልሆኑ የገለጹት አቶ አማረ፤ በሰው ኃይል፣ በሥልጠና፣ በማተሚያ ዋጋና በገንዘብ ረገድ ካሉት ችግሮች አኳያ አንዳንድ ጠንካራ የፕሬስ ውጤቶችን ማየት አበረታች እንደሆነ ተናግረው የመንግሥት በጐ ድጋፍ ታክሎበት ቢሆን ኖሮ ደግሞ ብዙ የተሻሉ ፕሬሶች ይታዩ እንደነበር ተናግረዋል።

የእኛ አገር ፕሬስ ከሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ፕሬስ ጋር ሲነፃፀር እዚህ ግባ የሚባል አይደለም ያሉት አቶ አማረ፤ እንደሚታየው የዜና ሽፋኖቻችን ከአዲስ አበባ ውጭ ሊወጡ አልቻሉም። በሕግ፣ በኢኮኖሚና በሌሎች ማኅበራዊ ጉዳዮች ለምሳሌ ሙስናን በመታገል ላይ ያለን ተነሳሽነት ዝቅ ያለ ከመሆኑ በላይ ራሳችንም ለሙስና የተጋለጥን መሆናችንን ማስተሐቀር አይቻልም" ነው ያሉት።

## <u>የፎርቹን ሣምንታዊ እንግሊዘኛ ጋዜጣ ባለቤትና ዋና አዘጋጅ አቶ ታምራት ገ/ጊዮርጊስ</u>

ይህንኑ የፕሬስ ሕግ በሚመለከት ያነጋገርናቸው የፎርቹን ሣምንታዊ እንግሊዘኛ ጋዜጣ ባለቤትና ዋና አዘጋጅ አቶ ታምራት ገ/ጊዮርጊስ ናቸው። አዲሱን የፕሬስ ሕግ እንዴት እንዳዩት ለጠየቅናቸው "አዲሱን የፕሬስ ሕግ ከተለያየ አቅጣጫ ማየት ይችላል" ይላሉ፤ "ለምሳሌ ከ1985ቱ የፕሬስ ሕግና አሁን መሆን ካለበት የኢትዮጵያ ሚዲያ የተጠያቂነትና ግልጽነት ባህል፣ እንዲሁም ካለፉት አምስት ዓመታት ጀምሮ በረቂቅ ደረጃ ከተኼደበት አኳያ ማነጻጸር ይቻላል። በመሆኑም ይኼ የፕሬስ ሕግ ጥሩ ነው አይደለም ብሎ ለመናገር ከምትነሳበት ቦታ ይወሰናል። ለምሳሌ የአሁኑ የፕሬስ ሕግ ከ1985ቱ የፕሬስ ሕግ የተሻለ ነው ሲባል ቀደም ሲል በፕሬስ ሥራ ለሚፈጠር የሕግ መተላለፍ የወንጀል ቅጣትን ሲያዝ የአሁኑ ግን አይዝም።

"በሌላ በኩል የ1985ቱ የፕሬስ ሕግና የፍርድ ሂደቱ ዝርዝር ነገር የሌለው ሲሆን በአሁኑ ሕግ ግን ዝርዝሩና ዓይነቱ በግልጽ ተደንግጐ ተቀምጧል። ከዚህ በተጨማሪ በአሁኑ ፕሬስ ሕግ ማንም ጋዜጠኛ ታስሮ መመርመርን ይከለክላል።በፊት ግን አብዛኛው ጋዜጠኛ የሚጉላላው በፍርድ ሳይሆን ታስሮ በሚመረመርበት ጊዜ ነው። እነዚህና ሌሎች የሕጉ አገባቦች ጥሩዎች ሲሆኑ፤ በኢትዮጵያ ነፃና ኃላፊነት የሚሰማውን ሚዲያ ለመፍጠር ከሚደረገው እንቅስቃሴ አኳያ ግን የሚቀሩት ነገሮች አሉ ብዬ አስባለሁ።" ይላሉ።

አቶ ታምራት በፀደቀው የፕሬስ ሕግ ላይ ካሉት በርካታ ችግሮች፤ ለዓቃቤ ሕግ የተሰጠው መጠነ ሰፊ ሥልጣንና መረጃ የማግኘት መብት ላይ የሰፈረው የአማርኛ

አጠቃቀም፣ ሰልፍ ሴንሰርሺፕ መሆኑን ይጠቅሳሉ "ጋዜጠኛው በሥራው ወቅት ይኸኛው ያስጠይቀኛል፣ ያኛው አያስጠይቀኝም በሚል የሃሳብ ብዥታ፣ መረጃን በተገቢው ሁኔታ ለመግለጽ ያዳግተዋል። ይኼ አካሄድ ደግሞ በሕገ መንግሥቱ የተከለከለውን ቅድመ ምርመራ የሚቃረን ነው" ካሉ በኋላ፤ "በሕጉ ውስጥ የተካተተው የፕሬስ ባለቤትነትን የተመለከተው ሕግ ሚዲያውን በተጠናከረ የሰውና የገንዘብ ኃይል ለማንቀሳቀስ የሚደረግን ጥረት በአጭሩ ገድቦታል" ብለዋል።

***በአዲሱ የፕሬስ ሕግ ጋዜጠኞች አይታሰሩም ሲባል ምን ማለት ነው?*** ለሚለው ጥያቄያችን አቶ ታምራት ምላሽ ሲሰጡ "ይኼን ጥያቄ ስታነሳ ፓርላማው መጨረሻ ላይ ያስገባቸው ሁለት ሕጎች ይወሳሉ። አንደኛው በፕሬስ የሚፈጸም የሞራል ጉዳትን ከ1000 ብር ወደ 100 ሺ ብር ከፍ ማድረጉ ነው። ይኼ ሕግ ለፕሬስ ብቻ መደንገጉ በጣም ያሳዝናል። አንዲት በመደፈር የተጠቃች ሴት በፍትሐ ብሔር ክስ ከስሳ የምታገኘው 1000 ብር ብቻ ሲሆን፣ በፕሬሱ ሕግ መተላለፍ ግን እስከ 100 ሺ ብር ድረስ ቅጣት መጣሉ የሕጉን ኢ-ሕጋዊነት ያሳያል።

"ሁለተኛ ማንም በፕሬስ በደል ደርሶብኛል የሚል ሰው፣ ጉዳዩ በቀጥታ በፍርድ ቤት በኩል ነው መታየት ያለበት ተብሎ ነበር። በኋላ ግን በፌደራል ዓቃቤ ሕግ ስር ክስ እንዲመሰረት ሥልጣን መሰጠቱ፣ ሕግ አውጭው አካል ለፕሬሱ ያለውን ጥሩ ያልሆነ አመለካከት ያሳያል። ከዚያ ውጭ ግን በፍትሐ-ብሔር ጉዳይ ብር እንድትከፍል ቢወሰንብህ ብር ትከፍላለህ፣ ከሌለህ ንብረትህ ይሸጣል ከሌለህ ግን የለህም ነው" ብለዋል።

***በዚህ ሁኔታ የፕሬሱ የወደፊት ዕጣ ፈንታ ምን ሊሆን ይቻላል?*** በሚል ግምታቸውን ጠየቅናቸው፤ ስለ ወደፊቱ ሁኔታ ለመገመት እንደማይችሉ ገልጸው "በአጠቃላይ ግን እንሠራለን፣ ተጠያቂነቱ ከመጣም በሕጉ መድረክ እናሸንፋለን ወይ እንሸነፋለን። በመሸነፋችን ጋዜጦቻችንን ወይም ድርጅቶቻችንን የሚያዘጋ ከሆነም እንዘጋለን" ብለዋል።

***ሕጉ የተለያዩ አገራት የፕሬስ ሕግን መሠረት አድርጎ የወጣው ነው ስለመባሉ ያላቸውን አስተያየት ጠይቀናቸዋል።*** ለጠየቅናቸውም "በእርግጥ አርቃቂዎቹ የተለያዩ አገራት የፕሬስ ሕግን እንደወሰዱ ተናግረዋል፤ ግን የየትኛውን አገር ወሰዱ ቢባል ምላሽ የለም። ለምሳሌ የአሜሪካንን ፕሬስ እንዳይባል ሚዲያ ላይ ሕግ እንዳይወጣ ሕገ መንግሥታቸው ይከለክላል። ስለዚህ የፕሬስ ሕግ የሚባል ነገር የለም። እንግዲህ አርቃቂዎቹ ሲናገሩ እንደሰማነው የአሁኑ የፕሬስ ሕግ ከስዊድን የተቀዳ ነው ይላሉ። ስዊድን ግን በዓለም ላይ ሃሳብን በመግለጽ ደረጃ ትልቅ ቦታ ያላት አገር ናት እንደውም ከአሜሪካን የተሻለ ሃሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ያላት አገር ናት ነው የሚባለው። የዚህ አገር የፕሬስ ሕግ ከየት እንደመጣ የሚያወቁት አውጪዎቹ ብቻ ናቸው" ብለውናል።

አቶ ታምራት በመጨረሻ እንዳወሱት ማንኛውም ሕግ የመጽሐፍ ቅዱስ ወይም የቁርዓን ቃል ባለመሆኑ እንደ ወቅቱ ሁኔታና ባለ ድርሻ አካላቱ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ሊሻሻል የሚችል ነገር እንደሆነ ጠቁመው፤ "ይህንም ሆነ ሌላውን ሕግ ለማስቀየር፣ የባለድርሻዎችን ስምምነት ይጠይቃል። አሁን በአገራችን አራት፣ አምስት የሚሆኑ የጋዜጠኛ ማኅበራት አሉ፤ ሁሉም ለአባላቶቻቸው የሚጠቅም ሥራ ቢሠሩ እንኳ በጥቅሉ ኢንዱስትሪውን ሊጠቅም የሚችል ነገር ሲሠሩ አይታይም። ባለፉት አምስት ዓመታት ረቂቅ የፕሬስ ሕጉን አስመልክቶ ከመንግሥት ጋር ተደጋጋሚ ውይይት እንደመደረጉ ጠንካራ የጋዜጠኛ መድረክ ባለመኖሩ ምክንያት ብዙ ዕድል አምልጦናል" ብለዋል።

## <u>የአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ አቶ ዳዊት ከበደ</u>

ሌላው አስተያየት ሰጪያችን በምርጫ 97 ከቅንጅት አመራሮች ጋር ታስረው የተፈቱት የአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ አቶ ዳዊት ከበደ ናቸው። አዲሱ የፕሬስ ሕግ ቀደም ሲል ከነበረው የፕሬስ ሕግ የሚለይበትንና የሚመሳሰልበትን አንዳንድ ነጥቦች እንዲያብራሩልን ጠየቅናቸው።

"አሁን የወጣው የፕሬስ ሕግ ከቀድሞው ሕግ ጋር ምንም የሚያገናኘው ነገር የለም። ስለ አሁኑ የፕሬስ ሕግ አስቸጋሪ አንቀጾች እነዚህ፣ እነዚህ ናቸው ብሎ ከመናገር ይልቅ ሕገ መንግሥቱን የሚጻረር የፕሬስ ሕግ ነው ማለቱ ይሻላል።ለምሳሌ በሕገ መንግሥቱ ሃሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ላይ ቅድመ ምርመራ የሌለ መሆኑን ቢገልጽም፣ በአዲሱ የፕሬስ ሕግ ግን ዓቃቤ ሕግ ጋዜጣውን ልከሰው  የሚያስችለኝን ጉዳይ አግኝቼበታለሁ ብሎ ከገመተ በቀጥታ  ከኅትመት ሊያግደው እንዲችል ሥልጣን ሰጥቶታል፤ ይኼ ማለት እንግዲህ አንድ ሃሳብ ወደ ህዝብ ከመሠራጨቱ በፊት የዓቃቤ ሕጉን ይሁንታ ማግኘት አለበት ማለት ነው።በአጠቃላይ የወጣው ሕግ ለትርጉም ክፍት የሆነና የኢትዮጵያን ፕሬስ ዕድገት ከማይመኙ ወገኖች የወጣ ሕግ ነው ማለት ይቻላል" ብለዋል።

በፕሬስ ሕጉ ላይ ውይይት መካሄዱን ከመንግሥት መገናኛ ብዙኃን ከመስማታቸው በቀር እነማን እንደተሳተፉ እንደማያውቁ የገለጹት አቶ ዳዊት "እርግጥ ነው በተካሄዱ ውይይቶች ጋዜጠኞች ተጋብዘዋል ወይም ተሳትፈዋል የሚባለው ለነሱ ቅርብ የሆኑ ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ፣ በኛ በኩል ግን ማንም ለውይይት አልጠራንም። ዓለም አቀፉ የጋዜጠኞች ተከራካሪ ቡድን (ሲፒጄ) ባወጣቸው መግለጫዎች በውይይቱ ወቅት የነፃው ፕሬስ ጋዜጠኞች አለመሳተፋቸውን ደጋግሞ ገልጿል" ነው ያሉት።

***አዲሱ የፕሬስ ሕግ እንደ በፊቱ ጋዜጠኛው ታስሮ መመርመሩን ያስቀረ መሆኑን በሚመለከት ምን አስተያየት እንዳላቸው ለጠየቅናቸውም*** ይኼ "አልሸሹም ዞር አሉ እንደሚባለው ነው። በቀድሞውም የፕሬስ ሕግ ጋዜጠኛ ታስሮ እንዲመረመር የደነገገ

አንቀጽ የለም። እኛ በጋዜጠኛነት ሙያችን፣ ሃሳብን በነፃነት በመግለጻችን፣ በጄኖሳይድ ክስ ተመስርቶብን ታስረን የነበረው ሕጉ ፈቅዶ እኮ አይደለም። በመሠረቱ በዚህ ሕግ ጋዜጠኛው፣ መታሰር ቀረለት ቢባልም እውነት እንዳልሆነ በሕጉ ውስጥ የተደነገጉትን ክልከላዎችና ቅጣቶች ማየቱ በቂ ነው" ብለውናል።

በአጠቃላይ አዲሱ የፕሬስ ሕግ ሃሳብን የመግለጽ ነፃነትን የሚገድቡ አንቀጾች የተካተቱበትና የኢትዮጵያን ነፃ ፕሬስ ጉዞ አደናቃፊ እንደሆነ አብዛኛው ጋዜጠኛ ይስማማበታል። ዓለም አቀፉ የጋዜጠኞች መብት ተከራካሪ ቡድንም ይህንኑ ሕግ በሚመለከት ለፕሬዝዳንት ግርማ ወልደጊዮርጊስ የተቀውሞ ደብዳቤ ጽፏል።

ይኼን አስተያየት ለማሰባሰብ በተንቀሳቀስንባቸው አጋጣሚዎች ያነጋገርናቸው ጋዜጠኞች አሳታሚዎችና አከፋፋዮች እንደተናገሩትም የአዲሱ የፕሬስ ሕግ መፅደቅ ለገዢው ፓርቲ ጠቦት የመስዋዕት ያህል ነው። በኢህአዴግ የፖለቲካ ፕሮግራም እንደተመለከተው አሁን ያለው ነፃ ፕሬስ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ተገዢ እንዲሆን መንግሥታዊ ጫና እንደሚደረግበት በግልፅ ደንግጎታል።

ይሁንና አዲሱ የፕሬስ ሕግ ግን በሥልጣን ላይ ያለው ፓርቲ ራሱ ከ15 ዓመት በፊት አፅድቆ ሥራ ላይ ካዋለው ሕግ የባሰ እንጂ የተሻለ እንዳልሆነ የሕግ ባለሙያዎችም እየተናገሩ ነው፤ አሁንም በሕጉ ላይ ለመምከር ጊዜው አልረፈደም።

## በኢትዮጵያ የሕትመት ሥራ ታሪካዊ መረጃ

ነጋሪት እየተጎሰመና እንቢልታ እየተነፋ "አዋጅ! አዋጅ!" ተብሎ ለህዝብ መረጃና የመንግሥት መልዕክት ይተላለፍባት የነበረች አገር ነች - ኢትዮጵያ። አባ ማሪያ በርናርድ የተባሉ ሚሲዮናዊ በ1983 ዓ.ም. አካባቢ "ላ ሰሜይን ዲ ኢቶፒ" (la semaine d'ethiopie) የሚባል ጋዜጣ በአማርኛና በፈረንሳይኛ ማሣተም ጀመሩ።

በአባ ማሪያ የተከፈተው ቀዳዳ ሰፍቶ አንድርያስ ካቫዲ የተባለው የግሪክ ነጋዴ "አእምሮ" የተሰኘ በእጅ እየተጻፈ የሚወጣ ሣምንታዊ ጋዜጣ እያዘጋጁ ማሠራጨት ሲጀምሩ የአንባቢው ቁጥር ከፍ በማለቱ በፖሊግራፍ ማተሚያ መሣሪያ መታተም ጀመረ። ኮፒውም ወደ 200 ከፍ በማለት እድገት አሳየ።

ከዚያም "የጦር ወሬ" የተሰኘ ስለመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ዘገባን የሚያቀርብ ጋዜጣ ታትሞ መሰራጨት ጀመረ። "ጎሕጽባህ" የተሰኘ ጋዜጣ ብላቴን ጌታ ኅሩይ አዘጋጅተው ሲያወጡ "አቶፒኮስ ኮስሞስ" (Aithopicos cosmos) የተባለ የግሪክ ጋዜጣ በ500 ኮፒ ታትሞ ይሠራጭ ነበር።

መረጃ በአግባቡ ካልተሠራጨ የኢትዮጵያን አንድነትና ዕድገት ማስጠበቅ እንደማይቻል ያመኑት አልጋወራሽ ተፈሪ መኮንን በ1914 ዓ.ም. በገነተልዑል ቤተመንግሥት በአሁኑ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ግቢ የህትመት ማሽን አስተክለው ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤትን አቋቋሙ።

አራት ተጨማሪ የማተሚያ መሣሪያዎች በተገዙ በአንድ ዓመቱ በ1917 ዓ.ም. በየሣምንቱ በሁለት ፈረሰኞች የሚከፋፈል 500 ኮፒ ብዛት ያለው "ብርሃንና ሰላም" የተባለ ጋዜጣ ታትሞ ይሠራጭ ነበር። ኢትዮጵያ በኢጣሊያ እስከተወረረችበት ጊዜ ድረስም "ብርሃንና ሰላም"፣ "አእምሮ"፣ "ከሳቴ ብርሃን" እና "አጥቢያ ኮከብ" የሚባሉ ጋዜጦች ታትመው ይሰራጩ ነበር።

ከድሉ በኋላም "ባንዲራችን" እና "ሰንደቅ አላማችን" የሚሉ ጋዜጦች ለህትመት ሲበቁ፣ በ1927 ዓ.ም. ደግሞ "አዲስ ዘመን"፣ በ1929 ዓ.ም. "ዘ ኢትዮጵያን ሄራልድ" (The Ethiopian Herald) መታተም ጀመሩ። በ1953 ዓ.ም. "መነን" እና "ቮይስ ኦፍ ኢትዮጵያ" (Voice of Ethiopia) የተሰኙ መጽሔቶች ታትመው መሠራጨት ጀመሩ።

ደርግ ሥልጣን ላይ ከወጣ በኋላ የግል ማተሚያ ድርጅቶች በአዋጅ ተወረሱ። የግል ጋዜጣና መጽሔቶችን አሳትሞ ማሠራጨት በጥብቅ በመከልከሉ። የፕሬስ ነፃነት ክፉኛ ታፈነ። ለ17 ዓመታት በዘለቀው የደርግ የሥልጣን ቆይታ የሕትመት ውጤቶችን አሣትሞ ማሠራጨት ይቅርና ጽሑፎችን በእጅ ይዞ መገኘት ወንጀል ሆኖ በመገኘቱ የሰዎች የመናገር፣ የመጻፍና የማንበብም ጭምር መብታቸው ተገፈፈ።

በ1983 ዓ.ም. ገዢው ፓርቲ ሥልጣኑን ከያዘ በኋላ የደርግ መንግሥት ለ17 ዓመታት በፕሬሱ ላይ የፈጸመው ግፍ "እንዳንገበገበው"ና ለነፃነት እንደታገለ አንድ አካል በ1985 ዓ.ም. የፕሬስ ነፃነት የሚደነግግ አዋጅ አወጣ። በርካታ የፕሬስ ውጤቶች ለሕትመት በቁ። አሁንም ከተመሳሳይ የ17 ዓመታት የሥልጣን ዘመን በኋላ ታሪክ ተደግሟል። እንደ ደርግ መንግሥት ጭርስኑ መጻፍ አትችልም ሳይሆን "ትችላለህ፤ ግን እኔ በምልህ ብቻ መሆን አለበት" የሚል አሳሪ ሕግ በማውጣት የፕሬስ ነፃነት ለ17 ዓመታት "ባለህበት ሂድ" ሲል ቆይቶ አሁን ደግሞ "ወደ ኋላ ሂድ" ጉዞውን ተያይዞታል።